ቺካጎ ኢትዮጵያ፡ ኢትዮጵያ ቺካጎ

*ከኣንድ ለናቱ*

መድከም ይኖራል፡፡ መድከም ደግሞ ጥፋት ሳይሆን ያለሃቅ ነው፡፡ ወጣትም ይደክማል፡፡ በእድሜ መድከም የተፈጥሮ ሃቅ በመሆኑ አንዳችም ሰው ሰራሽ ኪኒና አያበረታታውም፡፡ በተለይ የአእምሮ ድካም እድሜም ባይኖረውም በእድሜ የሚመጣው ክፉ ነው፡፡ የሰው ክምችት ነውና ኢሕ አ ፓ የደከሙ ወጣቶችም ባለ አድሜ ጠገቦችም ነበሩት፡፡ ሰሞኑን ወደ ሰባት የሚጠጉ ወገኖቻችን የሃሳብ ልዩነትን እንዴት ማስተናገድ ተስኖአቸው ላይ ታች ሲሉ ማስተካከያውን አግኝተዋል፡፡

የመጀመሪያዎቹ ከሃዲዎች ባንዳነት ቢጠሩ ተገቢ ስያሜ ነበር፡፡ ከጉያችን እንዳፈተለኩ ከጠላት ባላነሰ ጉዳት አድርሰውብናል፡፡ ለደርግ እየጠቆሙ አባሎቻችንን አሳርደዋል፡፡ ጠላትነታቸውን በሚገባ አሳይተውናል፡፡ ኢ ሕ አ ፓ (ሁለት) ብለው በአርማችንና በልሳናችን ሙግት አልገቡም፡፡ ደርግም ከተጠቀመባቸው በሁዋላ አውድሞአቸዋል፡፡

የሩቁን እንተወውና የቅርቡን አንጃ ብናይ "ኢ ሕ አ ፓ (ዴ) ብሎ ራሱን ይፋ አድርጎ ለመንቀሳቀስ ወስኖ ነበር፡፡ ትግሉ መሮአቸው ዲፕሬስ በመሆናቸው ነው እንዴ ብሎ የጠየቀኝ ሰው አለ፡፡ ጠያቂ የጠየቀኝ እውነትነት ቢኖረውም እንዴት የትላንት ወዳጆቼን ላጥላላ ብዬ ጥያቄውን ሸውጄ አለፍኩት፡፡ ዴ ብለው የተለዩን አራት የጎላ ስህተቶችን አይቼባቸዋለሁ፡፡ እነሱም ባይዋጥላቸውም በልባቸው እውነት ነው እንደሚሉኝ አልጠራጠርም፡፡ አንደኛው ጥፋታቸው በድርጅት ውስጥ ድርጅት መፍጠራቸው ነው፡፡ ይህ በማንኛውም የፓለቲካ ድርጅት በተለይም በኢ ሕ አ ፓ ይቅርታ የማያሰጠው ወንጀል ነውና ያየነው በዋዛ አልነበረም፡፡ ሁለተኛው ጥፋታቸው ለዲሞክራሲ መገዛት አለመቻላቸው ነው፡፡ ሁሌ የሚገርመኝ ዲሞክራሲያዊ አሰራርን ማስተማር የሚችሉ ምሁራን እንዴት የዲሞክራሲን ደንብ ማክበር ተስኖአቸው ፀረ-ዲሞክራሲ ሊሆኑ ቻሉ? ዲሞክራሲ የሚለው ብዙሃን ሁሌ አሸናፊ ናቸው ነው፡፡ ግን አናሳ ወይም ጥቂቶች የመደመጥ መብት እንዳላቸው የታወቀ ነው፡፡ ዴዎች የ80%(ያውም ቅር አንዳይላቸው አወፍሬው) ድምጽ እያለን እንዴት በርካታዎቹ እኛ ነን ለማለት እንደደፈሩ አስከ አሁን ያልተገለጸልኝ ነገር ነው፡፡ በሶስተኛ ደረጃ በኮንግረስ ወቅት ለሆቴል ክፍል፡ በቀን ሶስቴ ለበሉበት ምግብና ላንዳንድ ጥቃቅን ወጭ ለመሸፈን የገቡበትን ቃል ያስካዳቸው ስስት ይሁን ብልጠት ዛሬም ላውቀው ተስኖኛል፡፡ በትምህርትና በገንዝብ ከናንተ እንበልጣለን ብለው ትምህርቱንም ሃብቱንም ሲተገብሩ አለማየቴ ሳያስቀኝ አላለፈም፡፡ ባጭሩ ሜዳውንም ፈርሱንም ይዘው ብዙም ሳይጉኣዙ እነሱ ራሳችው ተፋረሱና ለብዙሃን መገዛት አልቻሉም ብለው በህጋዊ ድብዳቤ ካላቸው ቁጥር 45% አባረሩ፡፡ ኣስራ ምናምን ነበሩ ግን ወደ አምስቱን ሲያባርሩ ያምስቱ አንዳንድ ወዳጅ ተከትሎ በመውጣት አንጃውን የማይረባ አደረጉት፡፡ የተረፉትም ጉዳታቸውን ይዘው ወደ ሸንጎ ለመደበቅ ገቡ፡፡ የተባረሩትስ?

ሰሞኑን ደግሞ አንድ ጨዋታ ተከስቶ ነበር፡፡ ለነገሩ አርባ አመት የቆየ ድርጅት ጠላቱ ቢበዛ ያስገርማል እንዴ? ያለው መንግስት ዋና ጠላቱ ነው፡፡ የደከሙ ደግሞ ሳይወዱ ባቡሩ ይተፋቸዋል፡፡ ዴ ብለው የወጡት ስለ ሕግ የሚያውቁ ይመስለኛል፡፡ የሰሞኑ ሰባቶች ድርጅቱ በዲሲፕሊን ሲያባርራቸው ያደረጉት ግን ትእቢታቸውን ማዳመጥ ነበር፡፡ የድርጅቱን ስም እንዳለ ለመውሰድ ሞከሩ፡፡ የተቻላቸውን ማለትም አእምሮአቸው የፈቀደውን ተጠቅመው ሃቀኛውን ኢ ሕ አ ፓ ለመሆን ፈለጉና መግለጫ በስሙ ማውጣት ጀመሩ፡፡ ለካስፊደል በወጉ ካልተቆጠረ ወደ መቅለል ይወስዳል፡፡ የሚጽፉት ሁሉ ወያኔ ወያኔ ይሸታል፡፡ ወያኔዎቹ እንኩአኣን ሆዳም ምሁር በገንዘብ ገዝተው የሚያደናገር ጽሁፍ ይለቃሉ፡፡ የነዚኖዎቹ ድሮ እሪ በከንቱ ግራና ቀኝ ቆመው የሚሳደቡትን ልቅ የባለጊዎችን የሚመስል ስድብ በመልቀቅ ወደ እርጅናው የመጣባቸውን ባህሪ አሳወቁን፡፡ ከድርጅቱ እንደተባረሩ ልባቸው እያወቀው የእርምት አንቅስቃሴ የሚል ወግ ያዙ፡፡ እርማት ለማድረግ መጀመሪያ የራስን ገበና ማጽዳት ተገቢ ነው፡፡ ምነዋ ለዘመናት የአባልነት መዋጮ መክፈል ጠላችሁ? ምነው ድርጅቱ ለፈንድሬዚንግ ያሳተመውን ቲኬት ጥቂትም ቢሆን ሸጣችሁ ብሩን ፀጥ አደረጋችሁ? ለኮንፍረንስ አባላት ግዳጃቸውን በመወጣት የድርሻቸውን ሲከፍሉ ምነው አናንተ አለመክፈላችሁ?

ትናንት ቺካጎ ላይ ጉድ ሆናችሁ ሰማሁ። ለወጣቱ የተዘጋጅ ስብሰባችሁ ለአዛውንቱ ሆነ አሉ፡፡ ሕገ-ወጥ በመሆናችሁም አዳራሽ መከልከላችሁንም ሰማሁ፡፡ ንግግር ለማድረግ ሶስት ትሁኑ አራት ነበራችሁ፡። ቁጥራችሁ እንዲበዛ አራት ሁኑልኝ፡፡ አንጃው ካባረራቸው ደግሞ የናንተው ያህል ቁጥር ተገኝቶላችሁኣል፡፡ የውጭ ሰው ደግሞ ሁለት ይሁኑ ሶስት ነበሩ አሉ፡፡ አምጭ አምጬ ቁጥራችሁን ወደ አስራ አምስት ባስጠጋው ይጋነን ይሆን? ከሩቅ ስፍራ ማለትም ከሴንት ሉዊስና ከሚችጋን

ወገኖቻችሁም (ሁለት) ነበሩም ሰምቼ መስዋእትነታቸውን አደነኩ፡፡ ለማጠቃለል ያህል ሕዝባዊው ስብሰባ የናንተ ብቻ ሆኖ ቀረ አሉ፡፡ ባለመሳካቱ የትሳካ ስብስባ ይሉታል ይህ የናንተው ነው!

አንድ ትዝብት ተማርኩ፡፡ አፈንጋጮች ለምንድነው የድርጅቱን ብር መካድ የሚወዱት? አናሳ ሆነው አንደ ብዙሃን ተደማጭ ነን የሚሉት? ደግሞ ሌላ ጥፋት በሁላችሁም ላይ መኖሩ ትዝ አለኝ፡፡ ሽሽት ሲጀመር አመራሩን በተለይም ኢያሱንና ፋሲካን ጭራቅ ለማድረግ  የምትፈጥሩት ገጸ-ባህሪ ነው የሚገርመኝ፡፡ በነገራችን ላይ አናንተም (ምናልባት ሁላችሁም አትሆኑም) ልክ እንደ ዴ ስላምን አውጃችሁ ወደ ወያኔ ሳታስቡ አንዳልቀራችሁ አንዳንድ ምልክት አየታየ ነው፡፡ አላሙዲን ሃቀኛ ኢትዮጵያዊ ነው የሚሉ ከመካከላችሁ ወጣት ነን ባዮች እንዳሉ ተሰምተዋል (ዶላሩ ባይናቸው እየተሽከረከር)፡፡ ከእድሜ ጠገቦችም የበረከት ስሞዖን ወኪል እንዳገናቸውም ተስተውላል፡፡

ቺካጎ ሃቅኛ ድርጅትን ለማጥላላት ለተነሱት ጥቂት ሰዎች ትብብራችሁን ማገዳችሁ አኩርቶናል፡፡ ሃቀናው ኢ ሕ ኣ ፓ ከመሃከላችሁ በመገኘተ ወያኔ እንዴ ድባቅ መምታት እንደምንችል ለመምከር እንՊጣለን፡፡ እንዳለፈው መልካም መስተንግዶቻችሁን ናፍቀናል፡፡

ቀጣዩ ጉዞአቸው ወደ ዳላስ እንደሆን ከመካከላችሁ ውስጠ አዋቂ ነግሮናል፡፡ ልክ እንደ ቺካጎ ዳላስም ላይ የእፍረት ማቃችሁን ማግኘታችሁ አይቀርም፡፡ አንድ ምክር ልስጣችሁ፡፡ የበረከት ምክር በረከት ሳይሆን .እርግማን ነው፡፡ የአላሙዲን ብርም ሃብት ሳይሆን እከክ ያውም ነጭ አከክ . . . እና ትግሉን አታዋክቡ፡፡ ድርጅታችንም ለቀቅ አድርጉ፡፡ አለያ